ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)

34 ኛ ሳምንት

የቅዱስ ጴጥሮስ የመጀመሪያ ተአምር

ዓላማ

- ቅዱስ ጴጥሮስ በ *"መልካም መግቢያ"* ያደረገውን ተአምራት መማር፡፡

ምንባብ

- የሐዋ.ሥ 3

መግቢያ

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሠማይ ባረገ በ10ኛው ቀን፣ ደቀመዛሙርቱ ከእመቤታችን ጋር በተሰበሰቡበት ቤት መንፈስ ቅዱስ ወረደ ቤቱንም ሞላው፡፡

- ደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ በብዙ ቋንቋዎች መናገርም ቻሉ፡፡እንደታዘዙትም ወጥተው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማስተማር ጀመሩ፡፡በስሙም ብዙ ተዓምራት መፈጸም ቻሉ፡፡

- ዛሬ ቅዱስ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበለ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረገውን ተዓምር እንማራለን፡፡

ትምህርቱ

- አንድ ቀን ቅዱስ ጴጥሮስ እና ቅዱስ ዮሐንስ ለጸሎት ወደ ቤተ መቅደስ ይሄዱ ነበር፡፡ (ልጆች! ቤተ መቅደስ ምንድነው? ለመምህር አስረዱ፡፡)

- የቤተመቅደሱም መግቢያ ***"መልካሚቱ መግቢያ"*** ትባል ነበር፡፡በዚህች መግቢያ ከተወለደ ጀምሮ መራመድ የማይችል ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው በመልካሚቱ መግቢያ ተኝቶ ገንዘብ፣ ምግብ፣ ብር፣ ወርቅ፣ ልብስና ሌሎችም ስጦታዎች በልመና እየጠበቀ ይኖር ነበር፡፡ ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ መቅደስ ሲመጡ ተመልክቶም ምጽዋትን ለመናቸው፡፡

- ጴጥሮስ ከዮሐንስ ጋር ቆሞ በትኩረት ተመለከተው እና ***" ብርና ወርቅ የለኝም፣ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው፡፡"*** በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው፡፡ወዲያውም ሰውየው ተነሣና መራመድ ቻለ፡፡

- ይህ ሰው መራመድ በመቻሉ በጣም ተደሠተ፡፡እየዘለለና እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ፡፡ሕዝቡም እያመሰገነ ሲራመድ ሲያዩት ያውቁት ስለነበረ እግዚአብሔርን አመሠገኑ፡፡

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑት ብዙ ምልክቶች እና ተአምራት እንደሚከተሉአቸው ለደቀ መዛሙርቱ ነግሮአቸው ነበር፡፡ እንደነገራቸው ደቀመዛሙርቱ ብዙ ተዓምራትን መፈጸም ቻሉ አጋንንት አወጡ በሽተኞችንም ፈወሱ፡፡

ሙከራ

1. ጌታችን በአረገ በስንተኛው ቀን ነው ደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት?

_____

2. የቤተመቅደሱ መግቢ ምን ይባል ነበር?

_____

3. በዚያ ይለምን የነበረውን ሰው ቅዱስ ጴጥሮስ ምን አደረገለት?

_____

መዝሙር ተናገሩ ድንቅ ስራውን መስክሩ(2)
ተአምሩን ለዓለም ንገሩ(2)
ድንቅ ስራውን መስክሩ(2)

Peter's Miracle

ይቆየን፡፡